ቁጥር/Ref.No: ኢ.ሲ.ማ.ድ.ም/ቤ7 219/14
ቀን/Date: ነሐሴ 09/2014ዓ.ም.

# መግለጫ

## የኢፌዴሪ መንግስት እና ህወሃት ያሳዩትን ለድርድር ተነሳሽነት የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በማመስገን ሁለቱም ወገኖች በድርድር ሂደቱ ላይ በቅን ልቦና እንዲሳተፉ እያሳሰበ፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ለሂደቱ ድጋፍ ለማድረግ ምክር ቤቱ ዝግጁ እንደሆነ ይገልጻል።

***ነሃሴ 9, 2014, አዲስ አበባ፡-*** የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ጥቅምት 2013 የተቀሰቀሰው የትጥቅ ግጭትን ለመፍታት ከህዝባዊ ወያነ ሃርነት ትግራይ (ህወሃት) ጋር የሰላም ድርድር ለመጀመር የኢፌዴሪ መንግስት አደራዳሪ ኮሚቴ ማቋቋሙን ያበረታታል። በሁሉም ኢትዮጵያውያን ላይ ከፍተኛ ስቃይ ያስከተለውን ይህን ግጭት ለማስቆም ሁለቱም ወገኖች በሰላማዊ ድርድር ላይ ለመሳተፍ ያሳዩትን አወንታዊ እርምጃ ምክር ቤቱ ይደግፋል።

ከዚህም አንፃር ግጭቱ በድርድር እንዲቆም በሁለቱም ወገኖች የተስተዋለው ተነሳሽነት ሁሉንም የሀገሪቱን ዜጎች ተጠቃሚ የሚያደርግ ወሳኝ ውሳኔ ነው። ይህ ውሳኔ በተደራዳሪ ወገኖች ብቻ ሳይሆን ጉዳዩን በቅርበት እየተከታተሉ ባሉ በሁሉም ቁልፍ የሀገር ውስጥ እና የውጪ አካላት ከፍተኛ ትኩረት ሊደረግበት እንደሚገባ ምክር ቤቱ በጽኑ ያምናል።

በኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ዘርፉን የመወከል እና የማስተባበር ህጋዊ ስልጣን የተሰጠው ምክር ቤቱ እንደመሆኑ መጠን ለሰላም ያለውን ጠንካራ አቋም በተደጋጋሚ ከማሳወቁም በላይ ሁለቱም ወገኖች ልዩነታቸውን በድርድር እንዲፈቱ ጥሪ ሲያደርግ መቆየቱ ይታወቃል። የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት አሁን የተጀመረውን ጉዳዩን በሰላም የመፍታት ተነሳሽነት ሙሉ በሙሉ

እንደሚደግፍ እየገለጸ ጥረቱ የተሳካ እንዲሆን የሰላም ድርድር ሂደቱ ሁሉንም ቁልፍ ባለድርሻ አካላት በተለይም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ያሳተፈ ሊሆን እንደሚገባ በጥብቅ ያምናል። ይህም የሰላም የሰላም ድርድር ሂደቱ ቅቡልነት እንዲኖረው ከማድረግ ባለፈ ውጤቱ ዘላቂ ሰላምን ማረጋገጥ እንዲችል ከፍተኛ አስተዋጽ ያደርጋል።

ለዚህም ሁሉም አካላት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሰላም ሂደቱ ውስጥ በሁሉም ደረጃዎች ሊኖራቸው የሚገባውን ሚና ግምት ውስጥ እንዲገባና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሂደቱ ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ የአፍሪካ ሀብረት ኮሚሽን ድጋፍ እንዲያደርግ ምክር ቤቱ ይጠይቃል።

ስለሆነም የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት የትጥቅ ግጭቱን በድርድር ለመፍታት ለሚደረገው የሰላም ማስፈን ስራ ሙሉ ድጋፉን እንደሚሰጥ እየገለጸ በኢትዮጵያ ፍትሃዊና ዘላቂ ሰላም ለማምጣት በሚደረገው ሁሉ ለሰላም ግንባታው ሂደት የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት ያለውን ጥልቅ ቁርጠኝነት እና ዝግጁነት ያሳውቃል።

***<u>ስለ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት</u>***

*የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 1113/2011 በአንቀጽ 85 መሰረት የተቋቋመ ምክር ቤት ሲሆን በኢፌዲሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ተመዝግበው ዕውቅና ያገኙትን የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በሙሉ በመወከል በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲንቀሳቀስ በአዋጁ ኃላፊነት ተሰጥቶታል። በአሁኑ ወቅትም ከ3700 በላይ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የምክር ቤቱ አባላት ናቸው።*